ከሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል እና
ከኢትዮጵያ ዘውድ ምክር ቤት
የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

ጥቅምት ፲፫ ፲፱፻፺፯ ዓ.ም

ሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ከተቋቋመ አስራ ሶስት ዓመት ሁኖታል። በዚህም ለአገርም ሆነ ለድርጅቱ ፈታኝና አስቸጋሪ በሆኑ ዓመታት ውስጥ ብዙ ውጣ ውረድ ቢገጥመውም፣ ከተነሳበት ዓላማ ዝንፍ ሳይል፣ የኢትዮጵያ አርማ የሆነው ጥንታዊው ዘውድ በዘመናዊ መንገድ ተመልሶ እንዲቋቋም፣ በአገርም ሆነ በውጭ አገር፣ የሚያካሂደውን ትግል እንደቀጠለ ነው ።

በእነዚህ ከፍተኛ የትግልና የሥራ ዘመናት፣ ዘውድ በሕዝብ ህሊና ተቀርጾ የሚገኘውንና የሚኖረውን ሕልውና ዘለዓለማዊ ለማድረግ የተወሰዱት እርምጃዎች ሁሉ፣ መልካም ውጤት እንደማስገኘታቸው መጠን፤ ብዙ ክስተቶችንም ቁምር ያሳዩ ስለሆነ፤ ከነዚሁ ክስተቶች ትምህርት በመውሰድ አንዳንድ ለውጦችንም ለማድረግ አስገድደውናል። እነዚሁም ለውጦች ለሥራው የበለጠ ጥራትን፣ ለድርጅቱም ብርታትና ጥንካሬን ይጨምራሉ ብለን እንተማመናለን ።

ይህም ሲሆን፣ አሁን ያለው የሞዓ አንበሳና የዘውድ ምክር ቤት አውታር እንዳለ ሁኖ፣ በውስጡ በሰርጎ ገብነትም ሆነ በሥርዓት አልባነት ገብተው ድርጅቱን ለማሰናከል እሽክና አሜኬላ የሚዘሩ ግለሰቦች፣ ከድርጅቱ እንዲገለሉ መደረጋቸው ነው። ሥራው ከእንግዲህ ወዲህ የሚካሄደው በአዲስ ጉልበትና የሰው ኃይል ነው። አዲሱንም የወደፊት የሥራ እቅዳችንና ዓላማችንን በዝርዝር ለሕዝብ ከማስታወቃችን በፊት፣ የዘውዱንና የሞዓ አንበሳን የሥራ ኃላፊነት ስንረከብ የተነሳሳንበትን ዓላማና መሠረት እምነታችንን ባጭሩ እነደሚከተለው ለሕዝብ እንደገና እንገልጻለን።

፩ኛ፤ ዘውድ ነዋሪ የሕዝብ ቅርስ፣ መተዳደሪያና ሥነ ሥርዓት እንጂ፣ የአንድ ቤተሰብ የግል ንብረት እንዳልሆነ በሁሉም ዘንድ መታወቅ አለበት ።

፪ኛ፤ በዚሁም መሠረት፣ የዘውድ ባለቤት የሆነው ሕዝብ፣ ሥልጣኑ በእጁ ስለሆነ፣ ሊሰጥም፣ ሊያነግሥም፣ ሊሽርም የሚችለው ሕዝብ ነው ።

፫ኛ፤ የዘውድ አስተዳደር ለሕዝብ ጠቃሚ የሚሆነው ምንግዜም የሕዝብን ፍላጐት መዝኖ፤ ጊዜን ተከትሎ ሲራመድ ብቻ ስለሆነ፣ ሕዝብ በዲሞክራሲያዊ መልክ ለአስተዳደሩና ለእድገቱ በሚደረገው ሁሉ ተካፋይ በመሆን፤ በተለይም የፍትህና ርትእ ፍላጐቱና ሰብዓዊ መብቱ የተከበረና የተሟላ መሆን አለበት ።

፬ኛ፤ ዘውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት፣ ኃይሉና ክብሩ ከመሆኑም በላይ፣ እስካሁን አብሮት ከኖረው የእድገቱ መሠረት ስለሆነ፤ ከድህነት፤ ከበሽታና ከድንቁርና እንዲላቀቅ፣ እድገቱ እንዲጠብቅ ቅድሚያ መስጠት አለበት ።

፭ኛ፤ አንድ አገር፣ በሕዝቡ ሁሉ እኩልነት ካልተመሠረተ፣ አንድነቱ የማይፀና መሆኑን ከታሪክ እንረዳለን። ኢትዮጵያ ብዙ ነገዶችና ጐሣዎች የሚገኙባት አገር እንደመሆኗ፣ ሕዝቦቿ እስካሁን ለብዙ ዘመናት በትብብርና በመረዳዳት እንዳሳለፉት ሁሉ፤ ነገድና ጐሣን የመከፋፈያ ምክንያት ከማድረግ ይልቅ፣ የአገሪቱን የባሕልና የልማድ ብዛትና ብልጽግና የሚያበስር በማድረግ፣ ሁሉም በመደጋገፍ እንዲኖሩ፣ ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ እንዲሰፍን፣ ድርጅቶች ሁሉ ተሰባስበው እንዲመክሩበት ማድረግ ዋና ተግባራችን ነው ።

፮ኛ፤ እንደዚሁም፣ የልዩ ልዩ ሐይማኖት አማኞች ለብዙ ዘመናት በሰላምና በትብብር የኖሩባት ኢትዮጵያ፣ አሁንም ቢሆን እምነታቸው ተከብሮ፣ የአገሪቱን አንድነትና ሕልውና እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በሰላም አብሮ ለመኖር የሚያስችላቸው በሕዝብ ዘንድ በቂ ችሎታና እውቀት አለ ብለን እናምናለን ።

፯ኛ፤ የኢትዮጵያ የወደፊት ዕድል ሙሉ ዲሞክራሲ የሰፈነበት ዘመን ይሆናል ብለን ስለምናምን፣ የዘውዱ ሚና በሕግ የተወሰነ ወይም በውሬጡ አነጋገር (ኮንስቲቱሽናል ሞናርኪ) ስለሚሆን፣ ታሪካዊ ተግባሩም የሕዝቡ አንድነትና እድገት መሠረት ሁኖ ማገልገል ስለሆነ፣ ምንጊዜም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጠቃሚ የሆነ የታሪክ ቅርሱ መሆኑ

በሁሉ ዘንድ የታወቀ ነው ። ይህንኑ በመገንዘብ፣ የኢትዮጵያን ዘውድ ታሪክ ለማስከበርና ለማደስ ኃላፊ መሆናችንን በበኩላችን እያረጋገጥን፣ ለወደፊቱም በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገሮች፣ ለአገር እድገት ለወገን ኩራት፣ አስፈላጊውን ሁሉ ለማድረግ ቃል እንገባለን ።

በፕሮግራማችን ቅድሚያ የምንሰጣቸው ተግባሮች የሚከተሉት ናቸው ።

፩ኛ፣ ቀድሞ የተቋቋመው የዘውድ ምክር ቤት ሥራ፣ የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል እንቅስቃሴ፣ እንዲሁም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጐ አድራጐት ድርጅት፣ በአዲስ መንፈስና ጉልበት እንዲራመዱና እንዲስፋፉ በብዛት አባላትን መመልመልና ሥራዎቹን ማካሄድ ።

፪ኛ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነትና እድገት ከሐምሳ ዓመታት በላይ የአገልግሎት ዘመን ያበረከቱት፣ በመልካም ሥራቸው፣ በበጐ ምግባራቸውና በአርቆ አስተዋይነታቸው በዓለም ሁሉ አድናቆትን ያተረፉት፣ ኢትዮጵያንም በዓለም ዙሪያ እንድትከበርና ለጥቁር ሕዝብ ሁሉ አርአያ እንድትሆን ያበቋት ታላቁና ገናናው ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ፣ ታሪካዊ ለሆነው ታላቅ ሥራቸው፣ አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ፣ በግፍ ለተጨፈጨፉት መኳንንቶቻቸውም እንደዚሁም ።

፫ኛ፣ በኢትዮጵያ ምድር ውስጥ ካሉት የሃይማኖት፣ የፖለቲካ፣ የሞያተኛና የማህበራዊ ድርጅቶች እንደዚሁም ነገድ ጐሣ ትንሽ፤ትልቅ ሴት፤ ወንድ፤ ወጣት፤ ሽማግሌ ሳይባል፣ ከሁሉ ዜጋ ጋር ሰፊ ግንኙነት በመመሥረት፣ ለአገራችንንና ለሕዝባችን፣ የወደፊት እድገቱን የኑሮ መሻሻል የሚበጀውን ተባብረን አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ናቸው ።

የኢትዮጵያ የቀድሞ መሪዎች የሆኑት ነገሥታት፣ ለሕይወታቸው ሳያስቡ፣ ከሕዝቡ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘው በመራመድ፣ በቆራጥነት ባደረጉት አስተዋጽኦ፣ የአገራቸው አንድነት፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነትና ሰብዓዊ መብት እንዳይነካ፣ የውስጥም ሆነ የውጭ ጠላቶችን ተቋቁመው፣ ዳር ድንበር ሳይሸርፉ፣ ኢትዮጵያን ያስረከቡን ለሁላችን ስለሆነ፣ ሁላችንም የታሪክ ባለአደራዎች ነን ። ስለዚህ፣ የአባቶቻችንና የእናቶቻችንን አርዓያነት በአክብሮት በመከተል፣ ባለፉት ሐያ አራት ዓመታት ውስጥ በተጧጧፈው የፖለቲካ ውዝግብ ምክንያት፣ ዛሬ እጅግ ጐልቶ በሕብረተሰቡ መካከል የሚታየው የእርስ በርስ ጥላቻና አለመተማመን መሠረት የሆነውን፣ ለጠባያችን ባዕድ የሆነውን፣ የዘርና የጐሣ ወይም የጎጥ ስሜት የፈጠረውን የመለያየትና የክልል ግንብ አፈራርሰን፣ ባለፈው ይቅር በመባባል፣ ሕዝባችንን አስተባብረን፣ ኃላ ቀርነትንና ድሕነትን አስወግደን፣ እኩልነታችንን አምነንና አስከብረን፣ ታሪካችንን እንደገና ማደስ የእኛ የኢትዮጵያውያን ሁሉ ግዴታ ነው።

ይህንን ብሔራዊ ዓላማ ግብ ለማድረስና፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ በሙሉ ልብ ለማገልገል ዝግጁ መሆናችንን፣ እነሆ በታላቅ ትህትና ገልፀናል። የሕዝብ ፍላጐትና ድጋፍ፣ የቸሩ እግዚአብሔር ምህረታና ፈቃድ እንዲጨመርበት የዘወትር ፀሎታችን ነው። በእኩልነትና በአንድነት በመሥራት ሰላም በኢትዮጵያ እንዲሰፍን ቁልፍ የሆነ ሚና ለመጫወት የሚችለው ዛሬ በስደት ላይ የሚገኘው ወገናችን ሁሉ፣ አገሩ ተመልሶ ኢትዮጵያን በማገልገልና በመገንባት፣ የሕዝብ ረዳትና የወገን ኩራት እንዲሆን ሁላችንንም ምኞታችን ነው።

በመሆኑም፣ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ተሰባስበን የተለመደውን የኢትዮጵያ ሕዝብ አኩሪ ባሕልና ሥነ ምግባርን መሠረት አድርገን በመወያየት፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባላደራ የሆነውን ዘውድ መልሰን የምናቆምበት መላ እንድንወያይ ጥሪ እናደርጋለን። ለሁሉም እንዚአብሔር ይርዳን። አሜን።

ኢትዮጵያ ታበጽህ እደዊሃ ሐበ እግዚአብሔር

የሞዓ አንበሳ ሊቀ መንበር ዶክተር ጌታቸው መካሻ	የሞዓ አንበሳ ጠቅላይ ፀሐፊ አበበ ተስፋ	የዘውድ ምክር ቤት ፀሐፊ ሥዩም አበራ

MOA ANBESA
P. O. BOX 11403
ALEXANDRIA, VA 22312
USA